# ከተጭበረበሩ ምን ማድረግ እንዳለብዎ

Amharic




አጭበርባሪ ነው ብለው ለምታስቡት ሰው ከከፈሉ ወይም አጭበርባሪውን የግል መረጃዎን ወይም የኮምፒውተርዎን ወይም የስልክዎን መዳረሻ ከሰጡ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ይወቁ።

አጭበርባሪዎች በጣም አሳማኝ ሊሆኑ ይችላሉ። ገንዘባችንን ወይም እንደ ማህበራዊ ዋስትና ወይም መለያ ቁጥሮች የመሳሰሉ ሚስጥራዊነት ያለው ግላዊ መረጃችንን ለማግኘት ይደውሉልናል፡ ኢሜይል ይልኩልናል እንዲሁም የጽሑፍ መልእክት ይልኩልናል። እናም በሚያደርጉት ነገር ላይ ጎበዝ ናቸው። አጭበርባሪ ነው ብለው ለሚያምኑት ሰው ከከፈሉ ወይም የግል መረጃዎን ከሰጡ ወይም ወደ ኮምፒውተርዎ ወይም ስልክዎ እንዲደርሱ ካደረጉ ምን ማድረግ እንዳለብዎ እነሆ። ለአጭበርባሪ ከከፈሉ፣ ገንዘብዎ ቀድሞውንም ሊጠፋ ይችላል። ምንም ቢከፍሉ እንኳን፣ ገንዘቡን መልሰው የሚያገኙበት መንገድ ካለ ሁልጊዜ የተጠቀሙበትን ኩባንያ ገንዘቡን እንዲልክ መጠየቅ አስፈላጊ ነው።

## ለአጭበርባሪ ከከፈሉ

| | |
|---|---|
| የከፈሉት በክሬዲት ካርድ ነው ወይስ በዴቢት ካርድ? | ክሬዲት ካርድ ወይም ዴቢት ካርድየሰጠውን ኩባንያ ወይም ባንክ ያነጋግሩ። የተጭበረበረ ክፍያ እንደሆነ ይንገሯቸው። ዝውውሩን እንዲቀለብሱ እና ገንዘብዎን እንዲመልሱልዎ ይጠይቋቸው። |
| አጭበርባሪ ከባንክ ሂሳብዎ ያልተፈቀደ ማስተላለፍ አድርጓል? | ባንክዎን ያነጋግሩ እና ያልተፈቀደ ዴቢት ወይም ማውጣት እንደሆነ ይንገሯቸው። ዝውውሩን እንዲቀለብሱ እና ገንዘብዎን እንዲመልሱልዎ ይጠይቋቸው። |
| የከፈሉት በስጦታ ካርድ ነው? | የስጦታ ካርዱንየሰጠውን ኩባንያ ያነጋግሩ። በማጭበርበር ውስጥ ጥቅም ላይ እንደዋለ ይንገሯቸው እና ገንዘብዎን እንዲመልሱ ይጠይቋቸው። የስጦታ ካርዱን እራሱን እና የስጦታ ካርዱን ደረሰኝ ያስቀምጡ። |
| እንደ ዌስተርን ዩኒየን (Western Union) ወይም መኒግራም (MoneyGram) ባሉ ኩባንያ በኩል የኤሌክትሮኒክስ የገንዘብ ዝውውር አድርገዋል? | የኤሌክትሮኒክስ አአስተላላፊ ኩባንያውን ያነጋግሩ። የተጭበረበረ ዝውውር እንደሆነ ይንገራቸው። የገንዘብ ዝውውሩን እንዲቀለብሱ እና ገንዘብዎን እንዲመልሱልዎ ይጠይቋቸው።<br>• MoneyGram በ 1-800-955-7777<br>• Western Union በ 1-800-448-1492<br>• Ria (non-Walmart transfers) በ 1-877-443-1399<br>• Ria (Walmart2Walmart and Walmart2World transfers) በ 1-855-355-2144 |
| በባንክዎ በኩል የኤሌክትሮኒክስ የገንዘብ ማስተላለፍ አድርገዋል? | ባንክዎን ያነጋግሩ እና የተጭበረበረ ዝውውሩን ያሳውቁ። የገንዘብ ዝውውሩን እንዲቀለብሱ እና ገንዘብዎን እንዲመልሱልዎ ይጠይቋቸው። |
| በገንዘብ ማስተላለፍ መተግበሪያ በኩል ገንዘብ ልከዋል? | የተጭበረበረ ግብይትን ከገንዘብ ማስተላለፍ መተግበሪያ ጀርባ ለኩባንያው ያሳውቁ እና ክፍያውን እንዲቀይሩ ይጠይቋቸው። መተግበሪያውን ከክሬዲት ካርድ ወይም ዴቢት ካርድ ጋር ካገናኙት፣ ማጭበርበሩን ለክሬዲት ካርድ ኩባንያዎ ወይም ለባንክዎ ያሳውቁ። ክፍያውን እንዲቀይሩ ይጠይቋቸው። |

| | |
|---|---|
| በ cryptocurrency ከፍለዋል? | የክሪፕቶ ምንዛሪ ክፍያዎች በተለምዶ የሚቀለበሱ አይደሉም። አንዴ በክሪፕቶፕ ከከፈሉ ገንዘቦን መልሰው ማግኘት የሚችሉት የከፈሉት ሰው መልሶ ከላከ ብቻ ነው። ነገር ግን ገንዘቡን ለመላክ የተጠቀሙበትን ኩባንያ ያነጋግሩ እና የተጭበረበረ ግብይት እንደሆነ ይንገሯቸው። ከተቻለ ግብይቱን እንዲቀይሩ ይጠይቋቸው። |
| ጥሬ ገንዘብ ልከዋል? | በU.S. ሜይል ጥሬ ገንዘብ ከላኩ፣ የU.S. የፖስታ ቁጥጥር አገልግሎትን በ 877-876-2455 ያግኙ እና ጥቅሉን እንዲያጠለፉ ይጠይቋቸው። ስለዚህ ሂደት የበለጠ ለማወቅ፣ የ USPS መጥለፍ፡ መሰረታዊ (USPS Package Intercept: The Basics) የሚለውን ይጎብኙ።<br><br>ሌላ የመላኪያ አገልግሎት ከተጠቀሙ፣ በተቻለ ፍጥነት ያነጋግሩዋቸው። |

## የግል መረጃዎን ለአጭበርባሪ ከሰጡ

| | |
|---|---|
| የማህበራዊ ዋስትና ቁጥርዎን ለአጭበርባሪ ሰጥተዋል? | ክሬዲትዎን እንዴት እንደሚቆጣጠሩ ጨምሮ ምን እርምጃዎችን መውሰድ እንዳለብዎት ለማየት ወደ IdentityTheft.gov ይሂዱ። |
| የተጠቃሚ ስምዎን እና የይለፍ ቃልዎን ለአጭበርባሪ ሰጥተዋል? | አዲስ ጠንካራ የይለፍ ቃል ይፍጠሩ። ተመሳሳዩን የይለፍ ቃል ሌላ ቦታ ከተጠቀሙ፣ እዚያም ይቀይሩት። |

## አጭበርባሪ የኮምፒውተርዎ ወይም የስልክዎ መዳረሻ ካለው

| | |
|---|---|
| አጭበርባሪ የኮምፒውተርዎ የርቀት መዳረሻ አለው? | የኮምፒውተርዎን የደህንነት ሶፍትዌር ያዘምኑ፣ ስካን ያድርጉ እና እንደ ችግር የተለየውን ማንኛውንም ነገር ይሰርዙ። ከዚያ የግል መረጃዎን ለመጠበቅ ሌሎች እርምጃዎችን ይውሰዱ። |
| አንድ አጭበርባሪ የእርስዎን የሞባይል ስልክ ቁጥር እና መለያ ተቆጣጠረ? | የስልክ ቁጥርዎን እንደገና ለመቆጣጠር አገልግሎት ሰጪዎን ያነጋግሩ። አንዴ ካደረጉ በኋላ፣ የመለያዎን የይለፍ ቃል ይቀይሩ።<br><br>እንዲሁም ላልተፈቀዱ ክፍያዎች ወይም ለውጦች የእርስዎን ክሬዲት ካርድ፣ ባንክ እና ሌሎች የፋይናንስ ሂሳቦችን ያረጋግጡ። አንድም ካዩ፣ ለኩባንያው ወይም ለተቋሙ ሪፖርት ያድርጉ። ከዚያ ምን እርምጃዎችን መውሰድ እንዳለብዎት ለማየት፣ ወደ IdentityTheft.gov ይሂዱ። |

### ማጭበርበርን ለ FTC ያሳውቁ

ማጭበርበርን ሪፖርት ስያደርጉ፣FTC መረጃውን በአጭበርባሪዎች ላይ ክሶችን ለመመስረት፣ አዝማሚያዎችን ለመለየት፣ ህዝቡን ለማስተማር እና በማህበረሰብዎ ውስጥ ስላለው ነገር መረጃን ለማጋራት ሊጠቀምበት ይችላል። ማጭበርበር ካጋጠምዎት - ወይም አንድም እንኳ ካዩ በ

**ReportFraud.ftc.gov** ላይ ለFTC ሪፖርት ያድርጉ።

**ftc.gov/exploredata** ን በመጎብኘት በእርስዎ ግዛት ወይም ሜትሮ አካባቢ ምን እየተካሄደ እንዳለ ይመልከቱ።

FEDERAL TRADE COMMISSION
ጥቅምት 2022